በውሻ ሆድ ቅቤ አያድርም ።

ሰም ፡ ጌታው ፡ ቅቤን ቢያጠጣው ፤ ወይም ሰርቆ ቢበ
ላው ፤ ቅቤ ወዲያው ይወጣል እንጂ ፤ በውሻ ሆድ
ውስጥ አይውልም ፤ አያድርም ።

ወርቅ ፡ ቢአስፈራራትም ፤ ወይም ቢአባብሉትም እንኳ ፤
ምሥጢር በውሽታምና ትዕግሥት በሌለው ሰው
ሆድ ውስጥ ፡ በጥብቅ ተይዞ ፡ ወይም ተጠብቆ
ለብዙ ጊዜ አይኖርም ።

ወጥን ማን ያውቃል ፡- ቀላዋጭ ።

ሰም ፡ ወጥን ማን አሳምሮ ያውቃል ፡- ብዙ ዓይነት
ወጦችን በየቤቱና በየድግሱ እየዞረ ብዙ ጊዜ
የበላ ቀላዋጭ ሰው ነው ።

ወርቅ ፡ የማስተማርን ዘዴና የተማሪዎችን ጠባይ ማን
በጣም ያውቃል ፡- በማስተማር ሥራ ለብዙ ዓመ
ታት የቆየና እንዲሁም ልዩ ልዩ ጠባይ ካላቸው
ተማሪዎች ጋራ ብዙ ጊዜ አብሮ የኖረ ነባር አስ
ተማሪ ብቻ ነው ።

ወተት ለእንቦሳ ፡ ሥጋ ለአንበሳ ።

ሰም ፡ ሣርን መብላት ገና ላልጀመረ ለእንቦሳ ወተትን
ብቻ መስጠት ነው ፤ ሥጋውን ድቅቅ ፡ አጥንቱ

ንም ቁርጥምጥም አድርጎ መብላት ለሚችለው
ለአንበሳ ግን ሥጋን መስጠት ይገባል ።

ወርቅ ፡ ቢማርም እንኳ ፤ በአእምሮ ገና ላልበሰለና
የሥራ ልምምድም ለሌለው ለጎረምሳ በበታችነት
ዝቅተኛ ሥራ ብቻ መስጠት ነው ፤ በዕውቀት
ለደረጀ በዕድሜ መስተዋት ብዙ ነገርን ላየ
ለሸማግሌ ወይም ለጐልማሳ ግን በበላይነትና
በኃላፊነት ከፍተኛ ሥራን መስጠት የተገባና
የተፈተነም ነው ።

ከላይ ከደፈረሰ ከታች አይጠራም ።

ሰም ፡ ወራጅ ወይም የምንጭ ውሃ ከላይ ባለው ቦታ
በአንድ ምክንያት ከደፈረሰ ዘንድ ፤ ከታች በሚ
ገኘው ሥፍራ ላይ ምንም አይጠራም ።

ወርቅ ፡ በአስተሳሰብም ሆነ በአሠራር ከአባትና ከእናት
መልካም አርአያ ካልታየ በስተቀር ፤ ከልጆች
ዘንድ የባሰ ይሆናል እንጂ ፤ ለማኅበራዊ ኑሮ
የሚጠቅም ለሀገርም የሚበጅ ተግባር ከቶ አይ
ገኝም ።

ወርቅ ፡ ከሁሉ በላይ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ
ካልተፈቀደ በስተቀር ፤ ከሰማይ በታች ለመበል
ጸግም ሆነ የሕዝብም መሪ ለመሆን ምንም ቢሠሩና

ቢፍጨረጨሩ ፤ ይፈጸማል ፤ ማለት ከንቱ ድካም ብቻ ነው ።

ከቅርብ የወደቀ ፡ ከቍስል ዳን ።

ሰም ፡ አወዳደቅ ፡ የተለያየ ሁኔታ ስላለው ፤ ከቅርብ ቦታ ላይ የወደቀ ሰው ፡ ምንም እንኳ ለጊዜው ቢያመውም ቅሉ ፤ ከቍስል ይድናል ።

ወርቅ ፡ የቅጣት መጠን በወንጀሉ ስለሚለካ ፤ የበደል ሥራ የተለያየ ደረጃ አለው ፤ ስለዚህ ፡ አነስ ተኛ ጥፋት ያጠፋ ፡ ቢቀጣም ቅሉ ፤ ለብዙ ዓመታት ተፈርዶበት ከመታሠር ይድናል ።

ከወገኑ የተለየ አንበጣ ይሆናል ፌንጣ ።

ሰም ፡ ከወገኑ ፡ ወይም ከመንጋው ተለይቶ በአንድ ቦታ ላይ ተባራሪ ሆኖ የቀረ አንበጣ ፡ በገበሬዎች ዘንድ ፡ ከፌንጣ ተቆጥሮ ይናቃል እንጂ ፤ አዝመራን ያጠፋል ተብሎ ፡ አይፈራም ።

ወርቅ ፡ ከትውልድ ሀገሩ በአንድ ምክንያት ወጥቶ ፡ ከዘመዶቹም ተለይቶ በሰው አገር ላይ የሚኖር ሰው ባይተዋር ይሆናል ። ማንንም አምኖ ስለማይ ጠጋም ፤ ብቸኝነት ይሰማዋል ።

ከሁለት ቅርንጫፍ ያረፈች ወፍ ፡ ፪ ክንፏን ትነደፍ ።

ሰም ፡ ከሁለት ቅርንጫፎች ላይ ያረፈች ወፍ ፡ ለመ ብረር በምትነሣበት ጊዜ ፤ ሁለት ክንፎችዋን ትነደፋለች ።

ወርቅ ፡ በመዋጋትና ሸሽቶ በማምለጥ መካከል ላይ መንታ ሐሳቡን ያሳረፈ ወታደር ፡ ከሁለት አንዱን ሳይዘው ፤ በተማረከ ጊዜ ፤ ቆርጦ ባለ መዋጋቱ ፡ ወይም ሸሽቶ ባለማምለጡ ፡ ሲጸጸትና ሲያፍር ይኖራል ።

ወደሽ ከተደፋሽ ፤ ቢረግጡሽም አይክፉሽ ።

ሰም ፡ ብዙ ሰው ተጨናንቆ በሚወጣበት በር ላይ ወደሽ ድፍት ካልሽ ዘንድ ፤ እየተገፋፋ የሚወጣውም የሚገባውም ሁሉ ቢረግጥሽም ፤ መከፋት ወይም ማማረር የለብሽም ።

ወርቅ ፡ ጥፋትሽን እንድትተይ ፡ ጉድለትሽንም እንድታሚዪ ዘመድ ፡ ወዳጅ ቢመክርሽና ቢያስጠነቅቅሽ ፤ እንቢ ብለሽ ፡ ያንኑ የለመደብሽን አመል ስትቀጥዪ ፤ ቅጣት ፡ ወይም ጉዳት ፡ ቢደርስብሽ ፤ በደስታ መቀበል አለብሽ እንጂ ፤ዕድ

ልሽን መራገም ፡ ዘመዶችሽንም ማማረር ከቶ አይገባሽም ።

ያመኑት ፈረስ ፡ ይጥላል ከደንደስ ።

ሰም ፡ ያመኑት ፈረስ ፡ ምንም እንኳ ፡ አሳድገው ፡ ገርተው ፡ እየመጩኑ በደኅና ቢይዙትም ፤በጣም ከመጥገቡ የተነሣ ፡ ልቡን ሲነሣው ፤ አንድ ቀን ጌታውን ከደንደስ ላይ ክፉኛ መጣሉ አይቀርም ።

ወርቅ ፡ ብዙ ጊዜ ሳይታወቅበት ያለ ምሕረት የሚጐዳው ፡ ባልሆነ ቦታና ጊዜም ፡ በጭካኔ የሚጥለው ፡ ያመኑትና የወደዱት ሰው ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ወዳጅነቱን በማየት በብዙዎቹ ሰዎች ዘንድ ስለማይጠረጠር ነው ።

ዶሮ ብትታመም ፤ በግ አረዱላት ።

ሰም ፡ በአንድ ብር ከሰብዓ አምስት ሳንቲም የምትገዛ ዶሮ ፡ ብትታመም ፤ ቤዛ (ጭዳ) ይሆናት ዘንድ ወይም በሷ ፈንታ ተተክቶ እንዲሞት ዋጋው ኀምሳ ብር የሆነ በግን አረዱላት ።

ወርቅ ፡ ግምቱ ከሁለት ብር በማይበልጥ ጸብና ክርክር እንዲሁም ንዴትና እልህ ምክንያት ፤ ብዙ የሥራ ጊዜ ከመባከኑም በላይ ግርምቢጥ በሺሕ የሚቈጠር ብር ወጣ ። ይወጣልም ።

እንኳን ዘንቦብሽ ፡ እንዲያውም ጤዛ ነሽ ።

ሰም ፡ ልብስሽ በሙሉ እስቲበሰብስ ድረስ ፤ እንኳን ዝናብ ድንገት እላይሽ ላይ ዘንቦብሽ ይቅርና እንዲያውም ጤዛ (ቀዝቃዛ) ነሽ ።

ወርቅ ፡ አብዛኛው የሰው ልጅ እንኳን ተጣልተውት ፡ ምክንያት አግኝቶ ይቅርና ፡ እየወደዱትም ቢሆን የማንንም ስም ሆነ ብሎ ማጉደፍ ልማዱ ነው ።

አይጠቅም ጠላ ፡ ባልና ሚስት አጣላ ።

ሰም ፡ በሌላ ቀን ሁለተኛ የማይደገም ኃይለኛ ጠላ ፡ ደኅና ተስማምተው ይቀመጡ የነበሩትን ባልና ሚስት አሰከረና ክፉኛ አጣላ ።

ወርቅ ፡ እስተወዲያኛው የማያዛልቅና ለምንም የማይረባ ነገር ሁሉ ወዳጅን ከወዳጁ ፡ የበታችን ከበላዩ ፡ ሚስትን ከባልዋ ጋራ ሲያቈራርጥ ሲያለያይ ይኖራል ።

ወርቅ ፡ ከፍላጎቱና ከደስታው ጋራ ፡ በቅፅበት እንዳልነበረ ሆኖ የሚያልፈው ዓለም ፡ ሰውን በማይረባ ነገር እያታለለ ፡ የማያልፈውን መንግሥት ሰማያትን ያሳጣል ።

ይገርማል ! አህያና ዥብ ፡ አብሮ ይከርማል !

ሰም ፡ አህያና ዥብ በዱና ተበዱ ፡ ወይም አጥፊና ጠፊ ሲሆኑ ፤ አንድ ላይ መክረማቸው ፡ በጣም የሚ ገርም ነው !

ወርቅ ፡ በአንዱ ሰው ፡ ልብ ውስጥ ያለውን ሐሳብ ሌላው ሊያአውቀው ካለመቻሉ የተነሣ ፡ ያላ ወቀ ሰው ወዳጁ መስሎት ከጠላቱ ጋራ አብሮ መኖሩ ፡ በጣም ይገርማል !

ዶሮ ፡ ጭራ ጭራ ፡ ታወጣለች ካራ ።

ሰም ፡ ዶሮ ፡ ደመ ነፍስ እንጂ ፤ አእምሮ ያላት ፍጥ ረት ካለመሆንዋ የተነሣ ፡ የምትለቃቅመውን ለማግኘት ስትል ፤ እየጫረች ፡ የምትታረድበ ትን ካራ ታወጣለች ።

ወርቅ ፡ ሰው ፡ የብልግና ፍላጎቱን ለመፈጸም ሲል «አታመንዝር» የተባለውን ትእዛዝ እየጣሰ በሥጋው የሚቀጣበትን የመነካካት በሽታ በራሱ ላይ ያመጣል ።

አህያ ፤ ልጆችዋን ይዛ ብትጠፋ ፤ ዥብ የሚደፍራት አይመስላትም ።

ሰም ፡ አህያ ውርንጭላዎችዋን (ልጆችዋን) አስከትላ ከጌታዋ ዘንድ ብትጠፋና ፤ ወደ ጫካም ብት ገባ ፤ ጨካኙ ጠላትዋ ዥብ የሚደፍራት አይ መስላትም ።

ወርቅ ፡ ብድር መክፋፈል ፡ የማይቀር መሆኑን የሚዘ ነጋ ሰው ፡ በራሱ ትልቅነትና በወገኖቹም ተመ ክቶ ፡ ግፍ ቢሠራ ፤ ጡር ቢናገር ፤ ፍዳው ፡ ወይም ሞት ፡ ቀኑን ጠብቆ ፡ የሚደርስበት አይ መስለውም ።

የአዳኝ ውሻ ፡ ትርፉ ፡ ፀጉር ባፉ ።

ሰም ፡ አዳኝ ውሻ ፡ እያደነ የያዘውን አውሬ ለጌታው ማስረከብ ስለአለበት የሱ ትርፉ ወይም ዋጋው የያዘውን አውሬ ፀጉር በአፉ መቅረቱ ብቻ ነው።

ወርቅ ፡ አያገባው ገብቶ ባልና ሚስትን የሚያጣላ ሰው የኋላ ኋላ በስብቀቱ ያጣላቸው ባልና ሚስት ሲታረቁ ፤ ለእሱ የሚያተርፈው ፡ ቂምና በቀል ብቻ ነው ።

ከወገብ በላይ ታቦት ፡ ከወገብ በታች ጣያት ፤

ሰም ፡ ከወገብ በላይ ታቦት ፡ ከወገብ በታች ፡ ጣያት ሆኖ የተሠራ ምስል ቢኖር ፤ በሱ ላይ ያሉት ሁኔታዎች ፡ ተቃራኒዎች ናቸው ።

ወርቅ ፡ ባንድ በኩል ሰውን በሕይወቱ ሳለ ፤ ለመቅበር ጉድጓድን እየቆፈሩ ፡ በአንድ ፊት ደግሞ ወዳጅ ለመምሰል እህል ውሃ የሚሉ ሰዎች ቢኖሩ ፤ በነሱ የሚፈጸሙ ተግባሮች የማይስማሙ በመ ሆናቸው ፡ የክርስቲያን ሥራዎች አይደሉም ።

ባለቤቱ ፡ ካልጮኸ ፡ ጐረቤት ፡ አይረዳም ።

ሰም ፡ የሌባን መምጣት ሰምቶና አይቶ ወዲያው ባለ ቤቱ ፡ ካልጮኸ በስተቀር ፤ ጐረቤት ፡ የሆነ ውን ነገር ስለማያውቅ ፤ ፈጥኖ ሊረዳ አይች ልም ።

ወርቅ ፡ አሠሪ ወይም ቀጣሪ ሥራውን በቅርብ እየተከ ታተለ ካላሠራ በስተቀር ፤ ሠራተኞች ተቀጣ ሪዎች ከመሆናቸው የተነሣ ፡ ሥራውን እንደ ራሳቸው አድርገው ሊያከናውኑለት አይችሉም ።

ወርቅ ፡ በሽተኛ ወደ ሐኪም ዘንድ ኼዶ ፡ « እዚህ ላይ ያመኛል ፤ ይወጋኛል ፤ ያቃጥለኛል ፤ ወይም

የሚያመኝ ፤ ሆዴን ነው ፤ ራሴን ነው ፤ »ብሎ ካላመለከተ በስተቀር ፤ በሽታው ፤ በሐኪሙ ፍለጋ ብቻ በቶሎ ሊገኝለት አይችልም ።

ታሞ የተነሣ ፡ እግዚአብሔርን ረሣ ።

ሰም ፡ በጠና ታሞ ፡ ቆይቶ ፡ በኋላ ሲሻለው ከተኛበት አልጋ ላይ የተነሣ ሰው ፡ « የዛሬውን ማረኝ እንጂ ፤ ለወደፊቱ ግን ፡ ከቶ ከፈቃድህ አልወ ጣም ፤ » ይለው የነበረውን እግዚአብሔርን ፈጥኖ ረሳ ።

ወርቅ ፡ በድኽነት ሲቆራመድ ኖሮ ፤ ከጊዜ በኋላ ያለ ፈለት ሰው ፡ « አምላኬ ሆይ ! ከዚህ ከድኽነት ብታላቅቀኝ ፤ ችግረኞችን እረዳለሁ ፤ ባጭሩም እንደ አብርሃም እሆናለሁ ፤ » እያለ ይለምነው ይሳለው የነበረውን እግዚአብሔርን ወዲያው ከዳ ።

ትንሽ ቆሎ ይዛ ፡ ካሻሮጋ ትጠጋ ።

ሰም ፡ አጭበርባሪ ልጅ ፡ ተመልካቹን ለማደናገር እን ዲመቻት ፡ ጥቂት ቆሎ ይዛ አሻሮ አለበት ጋ ትጠጋለች ።

ወርቅ ፡ ብልጥ ሰው ፡ ወይም ብልጥ መንግሥት ፡ በረ ቀቀና አርቆ በሚመለከት ዘዴው ፡

አጠፋታውን ለመዝረፍ ፡ ያዘነ መስሎ አስቀድሞ ትንሽ ርዳታ ይዞ አንዱጋ ጠጋ ይላል ።

አንበሳ የሰበረው ፡ ለሹብ ይተርፈው ።

ሰም ፡ አንበሳ በልቶ ማብላት ልማዱ ስለሆነ ፤ አድኖ በማግኘት የሰበረው እንስሳ ለሰነፉና ለደካማው ለፈሪውና ለሆዳሙ ለሹብ ይተርፈዋል ።

ወርቅ ፡ አርበኞች ደማቸውን አፍሰው ፡ አጥንታቸውን የትም ከስክሰው ያስገኙት ነፃነት ለማንም ይተርፈዋል ።

አንተም ሌባ ፤ እኔም ሌባ ፤ ምን ያጣላናል በሰው ገለባ ፡-

ሰም ፡ አንተም ሌባ ነህ ፤ እኔም ሌባ ነኝ ፤ ታዲያ ያጋጠመንን ነገር ተስማምተን ለሁለት ሰርቀን ከቦታው ላይ ጥፍት እንደ ማለት ፈንታ ፡ በሰው ገለባ ምን ያጣላናል ፡-

ወርቅ ፡ እኔና አንተ ፡ በዚህ ዓለም ላይ በአንድነት ለጥቂት ጊዜ ቆይተን እንደ ጥላ ከነበርንበት ቦታ ላይ የምናልፍ ፡ ወይም የምንዛወር ስንሆን ፤ ተስማምተንና ተረዳድተን በመኖር ፈንታ ጥለነው በምንሄደው ነገር ሁሉ ምን ያፋጅናል ፡-

ነብር የሞተ ለት ፡ ፍየል ልጅዋን ትድራለች ።

ሰም ፡ ነብር ፡ የጥንትም ፡ ያሁንም ፡ የወደፊትም አጥፊዋና ጠላትዋ ስለሆነ ፤ እሱ የሞተ ለት ፍየል በጫካ ውስጥም ቢሆን ፡ ልጅዋን በደስታ ትድራለች ።

ወርቅ ፡ ጦርነት የሰላም ተቃራኒና የሰው ልጆችም አጥፊ ጠላት ስለ ሆነ ፤ እሱ ከምድር ገጽ የተደመሰሰ ለት የመላው ዓለም ሕዝብ ያለ ሥጋት በምቾትና በደስታ በኖረ ነበር ።

ተቀምጠ የሰቀሉት ፡ ቆሞ ለማውረድ ያስቸግራል ።

ሰም ፡ ተቀምጠ የሰቀሉትን ዕቃ ፡ እንደገና ቁጭ ብሎና ሥራ ፈትቶ ካልሆነ በስተቀር ፤ ቆሞ ፡ ወይም ፈጥኖ ለማውረድ ያስቸግራል ።

ወርቅ ፡ ልብ በሰብአዊ ርኅራኄ ሲነካና ሲሸነፍ ፤ ለሰው ያበደሩትን ፡ ብዙ ገንዘብ በውሉ መሠረት በሰላምና በፍቅር ተመልሶ ለመቀበል ያስቸግራል ።

ወርቅ ፡ በንዴት ወንበር ላይ ተቀምጠ ፡ ከፈጸሙት መጥፎ ተግባር ፡ ወይም አስቀድሞ መልሱን ሳያሰናዱ ፤ ድንገት ከተናገሩት ነገር በደኅና ለማምለጥ በጣም ያስቸግራል ።

ተኩላ እንደ አንበሳ እጮኻለሁ ብላ ተተረተረች ።

ሰም ፡ በተለያየ አኳኋን ጸንቶ መኖር የተፈጥሮ ሕግ መሆኑን የማታውቅ ተኩላ ልክ እንደ አንበሳ እጮኻለሁ ብላ ጩኸቱን ብትሞክር ፤ ተተር ትራ ሞተች ።

ወርቅ ፡ ዓቅሙን የማያውቅ ሰው የዚህ ዓለም ኑሮ የተለያየ መሆኑን በዓይኑ እያየ ፡ በአጉል መን ጠራራትና በእኩልነት ኑሮም ከሀብታሞች ጋር ለመወዳደር ሲል ፡ የገቢውን ዕጥፍ እያወጣ ፈጽሞ ደኸየ ።

አንገት ለምን ተፈጠረ ፡- አዙሮ ለማየት ።

ሰም ፡ አንገት ፡ ለምን ተፈጠረ ፡- ወደ ቀኝም ፡ ወደ ግራም አዙሮ ፡ ከወደ ኋላ የመጣውን ሁሉ ለማ የት ነው ።

ወርቅ ፡ አእምሮ ፡ ለሰው ልጅ ብቻ ለምን ተሰጠ ፡- ባለ ፈውና ኦሁንም ባለው ጊዜ ካገኘው ነገር ሁሉ ተምሮና ተመራምሮ ፡ ከክፋት ይልቅ ደግነትን ከቁጣ ትዕግሥትን ፡ ከበቀል ምሕረትን መርጦ ከይሉኝታ ጋር እንዲይዝ ብቻ ነው ።

ውሃን የሚያናግረው ደንጊያ ነው ።

ሰም ፡ ውሃን በየ ወንዙና በየሸንተረሩ ላይ ፡ ፏፏ ! እያሰኘ ፤ በግድ የሚያናግረው ፡ ደንጊያ ነው ።

ወርቅ ፡ ሰላማዊውንና ዝምተኛውን ሰው ፡ ክፉን ተና ግሮ ፡ የሚያናግረው ፡ መጥፎውን ሥራ ሠርቶ የሚያሠራው ፡ ነገረኛና ተንኳሽ ሰው ነው ።

ዓባይን ያላየ ፡ ምንጭ ያደንቃል ።

ሰም ፡ በውሃው ሙላትና ጥልቀት ፡ በያዘውም ቦታ ስፋትና ርዝመት ፡ በጣም ዝነኛ የሆነውን የዓባ ይን ወንዝ ያላየ ሰው ፡ ምንጭን ያደንቃል ።

ወርቅ ፡ እጅግ በጣም የሠለጠኑትን ሀገሮች እየዞረ ያላየ ሰው በሥልጣኔ ገና በማደግ ላይ የሚገ ኙትን ወጣት ሀገሮችን ያደንቃል ።

በፊት ከወጣ ጀሮ ፡ በኋላ የበቀለ ቀንድ በለጠ ።

ሰም ፡ በናቱ ማኅጸን ውስጥ አብሮ ከተወለደው ፡ ከእንስሳት ጀሮ ይልቅ ፡ እንስሶቹ ከተወለዱ በኋላ ፤ ጥቂት ወራት ቆይቶ የበቀለው ቀንድ በቁመት ፡ በጥንካሬና በውፍረት በለጠ ።

ወርቅ ፡ «ፊተኞች ፡ ኋለኞች ፡ ኋለኞችም ፡ ፊተኞች ይሆናሉ » እንደ ተባለው ፤ አስቀድሞ የሠለጠነው ሕዝብ ፡ ወደ ኋላ ሲቀር በሥልጣኔ ወደ ኋላ ቀርቶ የነበረው ግን ወደ ፊት ቀድሞ ኼደ ።

እንዳልውጠው ፡ ዓርብ ነው ። እንዳልተፋው እኽል ነው ።

ሰም ፡ የጐረስኩትን እንጀራ እንዳልውጠው ቀኑ ዓርብ መሆኑ ትዝ አለኝ ። እንዳልተፋው ደግሞ ያ የሰው ልጅ ሕይወት የሚሆነው እኽል ስለ ሆነ ፤በጣም ተቸግሬአለሁ !

ወርቅ ፡ የወለድኩት ልጅ በወላጅነት ግዴታዬ እንዳልወደውና እንዳላስጠጋው ፡ መጥፎና ባለጌ ሆነ ብኝ ። በጭራሽ እንዳላባርረውና እንዳልክደውም የሰውነቴ ቁራጭ በመሆኑ በጣም ችግር ብሎ ኛል !

መልካም ወጥ ፡ እጅን ያስመጥጥ ።

ሰም ፡ ምንም እንኳ ድርጊቱ ለተመልካች በጣም የሚያስጠላ ቢሆንም ቅሉ ፤ መልካም ወጥ ፡ እጅን ወይም ጣቶችን ያስመጥጣል ።

ወርቅ ፡ መልካም ሥራ ፡ ወይም መልካም ሃይማኖት ፡ ሰሚዎቹንና ተመልካቾቹን ከማስደንቁም በላይ ተጠራጣሪዎችን ወደማመን ፡ ክፉዎችን ወደ ደግነት ይመልሳል ።

ዕብድ ፡ ቢጨምት ፤ እስተ እኩለ ቀን ድረስ ነው ።

ሰም ፡ ከቀትር በፊት የሚያሰክሩትን መጠጦች ማግኘት እምብዛም ስለ ሆነ ፤ ዕብድ ሰው ቢጨምት፤ እስተ እኩለ ቀን ድረስ ነው ፤ ምክንያቱም ከእኩለ ቀን በኋላ ግን በዕብደት ላይ የመጠጥ ስካር ተጨምሮ ስለሚብስበት ነው ።

ወርቅ ፡ ከዳተኛ ባልንጀራ ፡ ከጓደኛውና ከወዳጁ ጋራ አብሮ መከራን ወድዶ የሚቀበለው ፡ እጅግ ቢበዛ፤ ብዙ ሀብትና ከፍተኛ ሹመት እስካለ ድረስ ብቻ ነው ።

ጊዜ የሰጠው ቅል ፡ ድንጋይ ይሠብራል ።

ሰም ፡ ምቹ ቦታ አጋጥሞት ፡ ጊዜ ወይም ዕድል ፡ ክብደትንና ጥንካሬን የሰጠው ቅል ፡ ከድንጋይ ጋራ ቢጋጭ ድንጋይን ይሰብራል ።

ወርቅ ፡ በሃይማኖትና በቅንነት አሠሪውን ከማገልገሉ የተነሣ ፡ መልካም አጋጣሚ አግኝቶ ያለፈለት አሽ

ከር ፡ እሱም በተራው ጌታውን በሠራተኛነት ቀጥሮ ይገዛል ።

የሆድ ብልሀት ፡ የጋን መብራት ።

ሰም ፡ በሥራና በንግግር ያልተገለጸ ብልሀት ፡ ወይም ትምህርት ፡ በጋን ውስጥ ሆኖ እንደሚያበራ መብራት ነው ።

ወርቅ ፡ ለትርፍ በንግድ ሥራ ፡ ወይም ለአስተዳደር በመንግሥት መሥሪያ ቤት ፡ ሳይሠራበት ፡ በማ ጥን ውስጥ ታጭቆ የተቀመጠ ጥሬ ገንዘብ ፡ ተበ ልቶ የማያጠግብ ፡ ተጠጥቶ የማያረካ ፡ ተለብሶ የማያሞቅ የሕልም ምግብና ልብስ ነው ።

ማሽላና ማሽላ ፡ ተያይዞ ቆላ ።

ሰም ፡ ማሽላና ማሽላ ማለት ፡ የማሽላ ዓይነት ዘር ሁሉ ጥሩ የሚሆነው ወይም የሚመቸው ፡ በቆላ አገር ብቻ ነው።

ወርቅ ፡ ጠጪና ጠጪ ፡ ግብራቸው ያው አንድ ስለሆነ፤ ተያይዞ ወደሚያቃጥለው ወደ መጠጥ ቤት መኼድ ብቻ ነው ።

ማቅ ፡ ያሞቃል ፤ ሻሽ ፡ ያደምቃል ።

ሰም ፡ ማቅ ፡ ምንም እንኳ መልኩ ባያምርም ቅሉ ፤ ከጸጉር የተሠራ በመሆኑ በብርድ ጊዜ ሰውነትን ያሞቃል ፤ ሻሽ ግን ሸክሙ ይቀላል ፤ በቀለሙም ያደምቃል ፤ ይሁን እንጂ ፡ ሰውን ከብርድ አያ ድንም ለሰውነትም ግርማ አይሰጥም ።

ወርቅ ፡ ደግ የሥጋ ዘመድ ፡ ምንም እንኳ ድኃ ቢሆንም ቅሉ ፤ በዝምድና ገመድ የተሣሠረ ከመሆኑ የተ ነሣ ፡ ደስታና መከራን አብሮ ይቀበላል ፤ ባዕድ ግን በጣም ይወደዳል ። ከእሱም ዘንድ የሚደበቅ ምሥጢር አይኖርም ፤ ይሁን እንጂ ፡ የኋላ ኋላ ፡ ከዳተኛና ፅኑ ጠላት የሚሆነው ፤ እሱ ብቻ ነው ።

ተላጭቶ ወለባ ፤ ልባልባ ታጥቆ ፡ አዛባ ።

ሰም ፡ ከተላጨ በኋላ ፤ በራስ ጠጉር ላይ ወለባን መሰካት አይቻልም ። ልባልባንም ታጥቆ ፡ አዛ ባን መዛቅ የሚስማማና የሚገባ አይደለም ።

ወርቅ ፡ ዓለምን በመናቅ ከመነኮሱ በኋላ ፤ በዓለማዊ ነገሮች ማጌጥና መሽቀርቀር ፡ የሚገባ አይደለም ። ልብሰ መነኮሳትንም ለብሶ ፡ በአጉል ቦታ ላይ መገኘት ያስነውራል ።

በጥባጭ ፡ ካለ ፤ ጥሩ አይጠጣም ።

ሰም ፡ መጠጥን የሚበጠብጥ ፡ ወይም የሚያደፈርስ መጥፎ ፍጡር ፡ ካለ ዘንድ ፤ ቁሻሻና ድፍርስ እንጂ ፤ ጥሩ መጠጥ አይጠጣም ።

ወርቅ ፡ ፀጥታን የሚነሣ ፡ ሕገወጥና አላኳሽ ፡ ካለ ዘንድ ፤ በጎብረቱ ሰብ ውስጥ ፡ ብጥብጥ እንጂ ፤ ሰላምና ፍቅር አይገኙም ።

በግ ፡ ባልበላሽ ፤ ትበዪኝ !

ሰም ፡ በግ ሆይ! ወይም አንቺ በግ ! በተፈጥሮ ባሕርይ ፡ እኔ በዪ ፤ አንቺ ተበዪ ስንሆን ፤ እኔ ሳልበላሽ ብቀር ግርምቢጥ አንቺ እኔን ትበዪኝ !

ወርቅ ፡ አንተ ሰውየ ! አንተ በዳይ ፤ እኔ ፡ ተበዳይ ስን ሆን እኔ በታጋሽነቴ ያልጠላሁህ እንደሆን ፤የተገ ላቢጠሽ ባንተ ብሶ አንተ ልትጠላኝ ይገባኻል ወይ ፡-

በሰም የተጣበቀ ጥርስ ፡ ቢስቁበት ፤ አያደምቅ ቢበሉበት ፤ አያደቅ ።

ሰም ፡ ከድድ ጋራ በሰም የተጣበቀ ጥርስ ፡ ከንፈሮችን ገለጥ ሲያደርጉ ፤ ማጣበቂያው ፡ ሰለሚታይ ፤

ቢስቁበት ፤ አያደምቅም ። ጠንካራ መሠረት የሌለው በመሆኑም ምግብን ቢበሉበት ፤ ከቶ አያደቅም ።

ወርቅ ፡ በገንዘብ ተገዝቶ ባል የሆነ ሰው ፡ አብሮ ቢቀመጥም ፤ የሚጠባበቀው ቀን እስቲወጣለት ድረስ ፤ ስለሆነ ፤ ቢወዱት ፤ ከልብ አያፈቅርም ። ሀብቱ የተጓደለ ጊዜም ፤ ሹልክ ብሎ ይሄዳል እንጂ ፤ ትንሽ እንኳ ለመቈየት አይግደረደርም ።

እጅ ፡ ሲያጣ ፤ ለአፍ ይጠናል ።

ሰም ፡ ምንም እንኳ እጅና አፍ ፤ ምንም የማይጨካከኑ ፡ ቢጨልምም የማይተጣጡ ቢሆኑም ቅሉ ፤ እጅ ቆርሶ የሚያጐርሰውን መብል ሲያጣ ፤ ሁልጊዜ ጉርሻን በደስታ ለሚያቀብለው ለአፍ ይጠናል ፤ (ይጨክናል ።)

ወርቅ ፡ ርኅሩኅ እናት ፡ ምንም እንኳ ለልጆችዋ ያላት ዕጉ ፍቅር ፡ መጠኑ ይህን ያህል ነው ፤ ሊባል ባይቻልም ቅሉ ፤ የሚቀመሰውን ያጣችና የነጣች ዕለት በልጆቿ ላይ ፡ መጨከንዋ አይቀርም ።

አላዋቂ ሳሚ ፡ ንፍጥ ይለቀልቃል ።

ሰም ፡ አላዋቂ ሳሚ ፡ በአሳሳም ጊዜ ጥንቃቄ ስለሚጐድ ለው ፤ የተሳሚውን ሰው ጉንጭ በንፍጥ ይለቀ ልቃል ።

ወርቅ ፡ ጉዳቱን ያልተገነዘበ ወላጅ ፡ የጠቀማቸው እየ መሰለው ፡ አረቄን ፡ ወይም ካቲካላን ለሕፃናት ልጆቹ እያጠጣ ያቃጥላቸዋል ። እንዲሁም ጥሬ ሥጋ እያበላ ፡ በኮሶ መዘዝ ያሠቃያቸዋል ።

ካልታጣ እህል ፤ ጓያ ሽመታ ።

ሰም ፡ በምግብነቱ በጣም የታወቀ ፡ ጤፍን ፡ ስንዴን ፡ የመሳሰለ ምርጥ እህል እያለ ፡ ለሰው ቀለብ እንዲ ሆን ፡ ጓያን መሸመት ፡ ከሞኝነት በቀር ሌላ ምክ ንያት የለውም ።

ወርቅ ፡ በመልካቸውና በውበታቸው ማማር ሥዕለ ማር ያምን የሚመስሉ ፡ በጠባያቸው ለሚስትነት የሚ በቁ ፡ ኢትዮጵያውያን ሴቶች እያሉ ፤ ወንደላጤ ሆኖ ፡ በገንዘብ እየገዙ ሴተኛ አዳሪዎችን ማመ ላለስ ፡ በብዙ መንገድ ይጐዳል እንጂ ፤ ከቶ አይ ጠቅምም ።

ገጣጣ ቢሞት ፤ የሳቀ ይመስላል ።

ሰም ፡ ገጣጣ ሰው ሲሞት ፤ ከንፈሮቹን ወዲያው ካላገ ጣጠሙአቸው ፤ ጥርሶቹ ስለማይከደኑ ፤ የሞተ ቢሆንም ፤ የሳቀ ይመስላል ።

ወርቅ ፡ ልበ ሰፊና ነገር አሳላፊ ሰው ፡ ምንም እንኳ በመ ጥፎ ድርጊት ፡ ወይም በመጥፎ ንግግር ቢቀየምና ቢናደድም ቅሉ ፤ ዓፀፋውን እስቲመልስ ድረስ ፤ ቁጣውን በትዕግሥት አሸንፎ የተደሰተ ይመ ስላል ።

የትም ፍጪው ፤ ዱቄቱን አምጪው ።

ሰም ፡ እኽሉን የትም ቦታ ሂደሽ በማንም ወፍጮ ልትፈ ጪው ይፈቀዳል ፤ ነገር ግን ከላዩ ላይ ምንም ሳይቀነስለት ዱቄቱን ማምጣት አለብሽ ።

ወርቅ ፡ የአገሬ ልጅ ሆይ ! የትም አገር ኼደህ ፡ በማንም ቋንቋም ትምህርቱን እንድትቀስም ይፈቀዳል ፤ ይሁን እንጂ የሀገርህን መልካም ባህሎችን መር ሳትና መናቅ የለብህም ።

ጸጉሜ ሲወልስ ፤ ጐተራህን አብስ ።

ሰም ፡ በጸጉሜ ፡ ደመናው ቢያንጐብብና ፡ ዝናቡም የጣለ እንደሆነ ፤ አዝመራው አምሮ ፍሬውን በብዙ ስለሚሰጥ ፤ ምርትህን እንድትከትበት ፡ ጐተራ ህን በደንብ ማበስ ፡ መጥረግና መለቅለቅ ነው ።

ወርቅ ፡ ዕድልህ ፡ አምሮ ፡ ወፍራም እንጀራ ወደ ቤትህ እገባ እገባ ቢል ፡ ትጋትህንና ደግነትህን ከበ

ፊቱ ይበልጥ ከፍ አድርጋቸው እንጂ ፤ ሀብቱ እንደሆነ ፡ አንዴ መጥቶ አል ፤ እኔም ከእንግዲህ ወዲያ ታውቂአለሁና ፤ ምን አደከመኝ ብለህ ጠጪና ባለጌ ፡ ትዕቢተኛና ጨካኝ መሆን የለብህም ።

የተግደረደረ ፡ ጦሙን አደረ ።

ሰም ፡ ሲበሉ ደርሶ ፡ «እኛን ምሰል!» ሲሉት ፤ ምንም ሳይበላና ምንም ሳይጠጣ ፤ «በቃኝ ! ጠግቤአለሁ ! » እያለ ፡ የተግደረደረ ሰው ፡ ሆዱን እያከከ ፤ ወይም ድፍት ብሎ ጦሙን አደረ ።

ወርቅ ፡ «ትምህርት ቤቶች ክፍት ሆነው ይጠብቁኻል!» ሲሉት ፤ የወላጆቹን ሀብትና ርስት ተማምኖ ፡ ከወርቅና ከዕንቁ የሚበልጠውን የትምህርትን ጥበብ በጊዜው ከመገብየት የሰነፈና የናቀ ሰው ፡ ዕድሜ ልኩን ተጐዳ ።

ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ።

ሰም ፡ የተሰጠው ተስፋ የማይፈጸም መሆኑ ሆድ ሲያውቅው « ማታ ዶሮ ትበላለህ ! » ብሎ ሰውን ማደፋፈር ፡ ዐዋቂ የማይቀበለው አነጋገር ነው ።

ወርቅ ፡ የተስፋው ቃል ወይም የወዳጅነቱ ንግግር ከለበጣ የመነጨ መሆኑን ልቡ ሲአውቀው ፤

«ፍጹም ታማኝህ ነኝ» ብሎ ሰውን ማግባባት አስተዋይ የማይቀበለው ሽንገላ ነው ።

ትልቁ ዳቦ ሊጥ ሆነ ።

ሰም ፡ ጥሩ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ የተንጓለለት ትልቁ ዳቦ በደንብ ሳይበስል ቀረና ሊጥ ሆነ ፤ ከዚህም የተነሣ ተመጋቢዎቹ ተሳቀቁ ።

ወርቅ ፡ ብዙ ጠቃሚ ነገሮችን ሳይፈጽም አይቀርም ፤ በሚል ግምት ከፍተኛ እምነት የተጣለበት ሰው ግምቱ የተሳሳተ ሆነና የባሰ መጥፎ ሆኖ ተገኘ ፤ ተጠባባቂዎቹም ተስፋ ቈረጡ ።

ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል ።

ሰም ፡ ሆድ በጽሞና ወይም በአዘቦት ቀን ደብቆት የነበረውን ነገር ብቅል ማለት የጠላ ስካር እያስለፈለፈ በግድ ያወጣዋል ።

ወርቅ ፡ ትዕግሥት በአስተያየት አልፎት የነበረውን የመጀመሪያ ስሕተት በድጋሚ የተሠራ አዲስ ጥፋት በይፋ እንዲታወስና እንዲገለጽ ያደርገዋል ።

አሞራው ፡ በረረ ፤ ቅሉም ፡ ተሰበረ ።

ሰም ፡ የፍየልና የበግ ግልግሎችን ፡ ዶሮዎችንና ጫጭቶችን ያስደነግጥ የነበረው አሞራ ርቆ ስለ በረረ

ወይም ስለ ሞተ ፤ የውኃን መልካም ቃና ያጠፋ የነበረውም ቅል ስለ ተሰበረ ፤ እንግዲህ ዓረፍን !

ወርቅ ፡ ጠላታችን ድንቁርና ፡ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ትምህርት ተወገደ ፤ ዐዋቂዎችንና ሕፃናትን በገፍ ይጠርግ የነበረውም የበሽታ ዓይነት ፡ በዘመናዊ ሕክምና ስለተዳከመ ፤ ደስታችን የበዛ ሆኗል !

እሳት ፡ ቢተኛ ፤ ገላባን ሰደደ ገበኛ ።

ሰም ፡ እሳት ለጊዜው ከመዳፈኑ የተነሣ ፡ የእሳትነቱን ጠባይ ቢተው ፤ ሰውየው ፡ የእሳቱ ገበኛ (አማካሪ) ይሆን ዘንድ ፡ ገለባን ላከ ።

ወርቅ ፡ የዘመኑ ወንዶች ፤ የባልነት ተግባራቸውን ዘንግተው ፡ ወንደላጤነትንና ሰውሠራሽ ሴትነትን ቢመርጡ ፤ ሴቶች ወደ ወንድነት ይለወጡ ዘንድ እግዚአብሔር ፡ ከፈጣሪነቱ ሥራ ጥቂቱን ብቻ ለሐኪሞች አካፈለ ።

ብርሌ ከነቃ ፤ አይሆንም ዕቃ ።

ሰም ፡ ብርሌ ፡ ከነቃ ፤ ወይም ከተሰነጠቀ ዘንድ ፤ በክርና በመርፌ ስለማይሰፋ ፤ በእርሳስም ስለማይበየድ ፤ የሚሳሱለት ዕቃ አይሆንም ።

ወርቅ ፡ ፅኑ ወዳጅ ፡ ወይም የትዳር ጓደኛ ፡ አንድ ጊዜ ከከዳ ዘንድ ፤ ምንም እንኳ ይቅርታን ቢለምንም

ቅሉ ፤ አድራጎቱ ሊረሳ ስለማይቻል ፤ እንደ መጀመሪያው እርሱን ለማመንና ለመውደድ በጣም ያስቸግራል ።

ጠጣ ፡ ባለቤቱን አስወጣ ። (ያስወጣ)

ሰም ፡ ጠጣ ገበሬዎች የደከሙበትን ሰብል ማጥፋት ልማዱ ስለ ሆነ ፤ የአዝመራውን ባለቤት ፡ ከሀገሩ ወይም ከሰፈሩ ላይ ስደት አስወጣ ፤ ወይም ያስወጣል ።

ወርቅ ፡ የቅኝ ገዢዎች ፡ የሰው አገር ሀብትን መዝረፍና ማሟጠጥ ፡ የሰውን መብት መቀማት ልማዳቸው ስለ ሆነ ፤ የሀገሩን ተወላጅ ከናት ሀገሩ ውስጥ እንዳባረሩ ይኖራሉ ።

ከወፈሩ ፤ አያፍሩ ።

ሰም ፡ ሰው ፡ ከወፈረ ዘንድ ፤ ብዙ ወታደሮች የጦር መሣሪያቸውን ይዘው ያጀቡት ስለሚመስለው ፤ የብዙ ሰዎች ዓይን አያሳፍረውም ።

ወርቅ ፡ ሰው ብዙ ጊዜ ወንጀልን ከሠራና የወንጀሉም ሥራ በሰውነቱ ውስጥ አድሮ ከተወሐደበት ዘንድ ፤ ይሉኝታ የሚሉት ሰብአዊ ዘበኛ ከሱ ጋ ተሰናብቶ ይኼዳል ። ከዚህም በኋላ የሰው ዓይን ምንም አያሳፍረውም ።

እንስራውን ጥላ ውሃ ወረደች ።

ሰም ፡ ውሃ የምታመጣበትን እንስራ ከቤት ትታ ፤ ውሃን ቀድታ ለመመለስ ወደ ወንዝ ወረደች ።

ወርቅ ፡ የጥያቄውን መልስ የምትጽፍበትን ብዕርዋን ወይም እርሳስዋን ረስታ ፤ ለመፈተን ወደ ፈተና አዳራሽ ገብታ ተቀመጠች ።

እንዶድ ፡ በገርነትዋ ውሃ ወሰዳት ።

ሰም ፡ እድፍን በማስለቀቅ ፡ ለሁሉም ሰው ታዛዥና ገር ዛፍ ከመሆኗ የተነሣ ፡ በየወንዙና በየምንጩ ላይ ልብስን ባጠቡባት ቊጥር ፤ ውሃ ሲወስዳት ይኖራል።

ወርቅ ፡ ደግ ሰው ቅንና ትክክለኛ ከመሆኑ የተነሣ ሌላ ውንም ሰው እንደራሱ እያየ ስለሚያምነው ፤ ተንኰለኞች እያታለሉ ሲጐዱትና ፤ ገንዘቡንም ሲወስዱበት ይኖራሉ ።

እንዳያማ ፡ ጥራው ፤ እንዳይበላ ፡ ግፋው ።

ሰም ፡ ግብጥ በምታደርግበት ጊዜ የማትፈልገውን ሰው « ከሰው ሁሉ ለይቶ ተወኝ » ብሎ እንዳያማህ ጥራው ። በምግብ ቤቱ ገብቶ እንዳይበላና እን ዳይጠጣ ግን ግፋውና ተቆጥቶ ይኼድልኻል » ማለት ነው ።

ሲተኙ ፤ ነገር ያገኙ ፤ ሲነሡ ፤ ነገር ይረሱ ።

ሰም ፡ ጸጥ ያለ ሌሊት የሐሳብ ማጣሪያ በመሆኑ ፤ ሲተኙ ነገር ይገኛል ። ቀን የተረሳውም ሐሳብ ይታወስ በታል ፤ ቀን ግን ዓይን የማይሰበሰብበት የሐ ሳብ ማባከኛ ስለሆነ ፤ ከመኝታ ላይ ሲነሱ በሌ ሊት የታሰበው እንኳ በማስታወሻ ካልተያዘ በስተቀር ፤ ወዲያው ይዘነጋል ።

ወርቅ ፡ መጥፎ ነገር ባጋጠመ ጊዜ ፤ ሲታገሡና ውለው ሲያድሩ ፤ ቁጣ ይበርዳል ። የተደበቀ ነገር ቢኖር ይገለጻል ፤ ጥሩ ምክርም ይገኛል። ወንጀል አይሠራም ፤ በንዴት ሲነሡና እንድን ነገር በጥድፊያ ሲሠሩ ግን ፤ ድንገት ስሕተት ይፈጠራል ። ሕግ መኖሩም ይዘነጋል ።

የሺ ፍልጥ ፡ ማሠሪያው ልጥ ።

ሰም ፡ የሺ ፍልጥ ማሠሪያው ልጥ ከሆነ ዘንድ ፤ ልጡ ሲደርቅ መሰበሩ ፤ ፍልጡም መበተኑ ስለማ ይቀር ፤ ትርፉ ከንቱ ድካም ብቻ ነው ።

ወርቅ ፡ በድንግልና የመመንኮሱ ጉዳይ እያያዙ ከላላና መጨረሻውም ካላማረ በስተቀር ፤ ትርፉ የጋብ ቻን ጊዜ በከንቱ ማባከን ብቻ ነው ።

ወርቅ ፡ ይጠላኛል ወይም ስለኔ ግድ የለውም ብሎ እንዳ
ይጠራጠር ወዳጅ መስሎ የግል ርዳታና ስጦታ
ማድረግ ፤ እንዳይደሰትም በስውር የሰውን ጥቅም
ማሰናከል ከቶ አይገባም ማለት ነው ።

ወርቅ ፡ ለጊዜው እንዳይቀየም ፡ ከአጠገብም እንዲሄድ
የማይፈጸመውን ተስፋ ለማንም ሰው መስጠት ፡
ለማይገኘውም ነገር ማንንም በቀጠሮ ማመላለስና
ሥራን ማስፈታት ከቶ አይገባም ማለት ነው ።

ፍየል መንታ ትወልድ ፤ አንዱ ለወናፍ አንዱ ለመጽሐፍ ።

ሰም ፡ ፍየል መንታ ግልገሎችን ትወልዳለች ፤ ይሁን
እንጂ የአንዱ ቆዳ የእቶን ወናፍ ሲሆን ፤ የአ
ንዱ ቆዳ ደግሞ የቅዱስ መጽሐፍ ብራና ይሆ
ናል ።

ወርቅ ፡ እናት ከአንድ ባልዋና ከአንድ ማኅጸንዋ ብዙ
ልጆችን ትወልዳለች ፤ ነገር ግን ከነሱ መካከል
አንዱ ድኻ ፤ አንዱ ሀብታም ፡ አንዱ ክፉ ፡ ሌላው
ደግ አንዱ ረኹም ፡ አንዱ አጭር ፡ አንዱ ንጉሥ ፡
ሌላው ዜጋ ፡ ወዘ . ይሆናሉ ።

ፈሪን ከውሃ ውስጥ ያልበዋል ።

ሰም ፡ ፈሪ ሰው ፡ ያለ መጠን ስለሚደነግጥ ፤ በቀዝ
ቃዛ ውሃም ውስጥ ገብቶ ቢቆመጥ ፤ ያልበዋል ።

ወርቅ ፡ ቁፈፋን የለመደ ሰው ፤ ምንም እንኳ መጠን
በሌለው ሀብት ውስጥ ቢዋጥም ቅሉ ፤ ምጽዋት
መለመኑን ፈጽሞ አይተውም ።

ፌንጣ ብትቆጣ ፤ እግሯን ጥላ ኼደች ።

ሰም ፡ ፌንጣ ከምትሸመጥጠው ሰብል ውስጥ ለምን
ተባረርኩ ብላ ፡ ተቈጣችና ለሞትዋ ፡ እግሯን
ጥላ ኼደች ።

ወርቅ ፡ ሐሳበ ውሱን ሰው ፡ በተናደደ ፤ ጊዜ ፡ ማንን
ጠቅሞ ማንን እንደሚጐዳ ሳያመዛዝን ራሱን
በራሱ ገደለ ፤ ወይም ይገድላል ።

የአብዬን እከክ ፡ ወደ እምዬ ላክክ ።

ሰም ፡ የአብዬን እከካምነት ወደ እምዬ ወስዶ በውሸት
ላክክ ማድረግ ነውር በመሆኑ ኮቶ አይገባም ።

ወርቅ ፡ ምንም እንኳ የማይገባ ነገርና ትልቅ ኃጢአት
መሆኑን አሳምሮ ቢያውቅም ፤ ምቀኛና ክፉ
ሰው የራሱን ጉድለትና ጥፋት በንጹሑ ሰው

ላይ መለጠፉና መላከኩ ምን ጊዜም ቢሆን የተለ መደ ነው ።

ችቦን ሲወጉ ፤ በአህያ ይጠጉ ።

ሰም ፡ ችቦን በጦር ወግቶ ፡ ወይም ጥይትን ተኩሶ ለመ ግደል ሲአስፈልግ ፤ የሚረዳ ዘዴ አህያን መኪታ ማድረግ ብቻ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ችቦ መብ ላቱን እንጂ ፤ መሞቱን ስለማያስብ ነው ።

ወርቅ ፡ ጠላትን በስውር ለመጉዳት ሲያስፈልግ ፤ የሚ ጠቅመው ብልሃት የሱን ፅኑ ወዳጅ ወይም ብርቱ ወዳጅነትን መሣሪያ ማድረግ ብቻ ነው ፤ ምክን ያቱም ፡ በወዳጁ ላይ ሊጠራጠር ስለማይችል ነው ።

ፍየልም የለኝ ፤ ከነብር ፡ ምን አጣላኝ !

ሰም ፡ እኔ ለራሴ ፍየል የለኝም ፤ ታዲያ ለባለ ፍየል ረድቼ ከነብር ጋራ ምን አጣላኝ !

ወርቅ ፡ እኔ ከሰውየው ጋራ ጥል ፡ ወይም ቂም የለኝም ! እንግዲያ ቂልነቱ ካልሆነ በስተቀር ፤ ለጥለኛው ተደርቤ ካልበደለኝ ሰው ጋራ ምን አጣላኝ !

የአባት ፡ ሞቱን አይወዱ ፤ ረጅቱን አይሰዱ ።

ሰም ፡ ከትትክለኞች ሰዎች መካከል የአባቱን መሞት የሚወድ አይገኝም ፤ አባቱ ፡ ከዚህ ዓለም ላይ

በሞት ከተለየ በኋላ ግን ፤ የአባቱን ሀብት ከመ ውረስ የሚቦዝን ከቶ የለም ።

ወርቅ ፡ ራሱም ሰው ነውና ፤ ሰዎች በየ ቀኑና በየ ሰዓቱ በሞት እንዲያልቁ የሚሻ አይገኝም ፤ ነገር ግን የሬሣን ሣጥን ቶሎ ቶሎ እየሸጠ ፤ በመነገድ ገንዘብን አትርፎ ለመበልጸግ የሚጠላ የለም ።

ጉፋያ ከመብላት ፡ ጮማ መሸከም ።

ሰም ፡ ጉፋያ ሥጋን እስቲጠግቡ ድረስ ፤ ከመብላት ይልቅ ፡ ጮማ ሥጋን መሸከም ይሻላል ፤ ምክ ንያቱም በዓይን ሲያዩት ስለሚያጠግብና ፤ የተሸ ካሚም በትንሹ ቅምሻ ስለሚበሉለት ነው ።

ወርቅ ፡ ወላጆቹን የሚአሰድብ መጥፎ ልጅን ወልዶ በመከባከብ ከማሳደግ ይልቅ ፡ ብሩክ የሆነውን የሰውን ልጅ በሚገባ ማሳደግ ይሻላል ።

ምንም ብቀጥን ፤ ጠጅ ነኝ ።

ሰም ፡ ጠጅ ጣዮችን እጃቸውን ከውሃው ነጠቅ አድርጎ አቸው ፡ ምንም ብቀጥንም እንኳ ፤ ጠጅ ነኝ ፤ ስለዚህ ከጠላው ሳልሻል አልቀርምና ፤ ችላ አትበለኝ ፤ አለ ጠጅ ።

ወርቅ ፡ የዕድል ፡ ወይም የአጓጉን ጉዳይ ሆኖ ምንም ብደሽይም እንኳ ፤ የጨዋ ልጅ ነኝና በማ ይገባ እኔን ማቋሸሽና መናቅ የለብህም ።

አገባሻለሁ ያለሽ ፡ ላያገባሽ ፡ ከባልሽ ኾድ አትባባሽ ።

ሰም ፡ በኋላ የሁሉም እንደ ሆኑ እንደ ሴትኛ አዳሪዎች ቁጥሮ እርስዋን መለስ ብሎ ላለማየት ፡ ባልዋ በማዕርግ ይዞ በልብስና በጌጥ ሌላ ነገር ሲያስ መስላት አይቶ ፡ ከሞቀው ቤትዋ ለማስወጣት ፡ ከደመቀው ኑሮዋ ላይ ለመታጣት ፡ የሰውን ሚስት ማባበልና ማታለል የምቀኛና የሰይጣ ናዊ ወንድ ልማድ ስለሆነ ፤ « ባልሽን ፍቺና አገ ባሻለሁ » ፤ ያለሽ ሰው ፡ በኔም ላይ ይሽው ናት ፤ ብሎ ላያገባሽ ፡ እንደ ኩስታራ ሴት ተጠንቀቂ ታማኝነትሽንና ጨዋነትሽን ጠብቂ እንጂ ፤ ከባ ልሽ ጋራ ኩቶ ሆድ አትባባሽ ።

ወርቅ ፡ ነፍሴ ሆይ ! በሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላውን መጥፎ ሥራ በየጊዜው ትሠሪ ዘንድ የሚገፋፋሽ ያንቺ ሥጋ ኩቶ አያዛልቅሽም ። ለራሱም ወደ መሬት ተመልሶ አፈር ከመሆኑ በስተቀር ከመኰነን አያድንሽምና ፤ ወደማይቀ

ሩበት የሞት ድግስ እስክትጠሪ ድረስ ፤ ከኃጢ አት ርቀሽ ለጥቂት ጊዜ ቆይ እንጂ ፤ ከፈጣሪሽ ጋራ በክፋትሽ እንዳትቈራረጪ ልብ አድርጊ !

ሕፃንን ፡ ምግብ ፡ እንጂ ፤ ስሞሽ ፡ አያሳድገውም ።

ሰም ፡ ሕፃንን እያፋፋ በጤንነት የሚያሳድገው በሐ ኪም ለሕፃናት የታዘዘውን ምግብ ብቻ ቢሚ ገባ መመገብና በጥንቃቄም መያዝ ነው እንጂ ፡ በየደቂቃው በሚስሙት ስሞሽ አይደለም ።

ወርቅ ፡ ሠራተኛን እየገፋፋ ሥራውን ከልብ የሚያሠ ራውና የሚያበረታታው ፡ ከኑሮው ደረጃ ጋር የሚመጣጠነውን በቂ ደመወዝ በጊዜው መክ ፈል ነው እንጂ ፤ « አይዞህ ! » የሚለውን የተስፋ ቃል ብቻ በማሰማት አይደለም ።

የጨሰ የጨሰውን ከወረወርሽው ፤ ምኑን ማገድሽው ፡-

ሰም ፡ ዕንጨት ሆኖ የማይጨስ ስለ ሌለ ፤ እሳትን በም ታነጂበት ጊዜ የጨሰ የጨሰውን ዕንጨት ሁሉ ልቅም አርገሽ እያነሣሽ ከወረወርሽው ፤ ታዲያ ምኑን ማገድሽው ፡-

ወርቅ ፡ ትምህርት ሲባል ፤ ሁሉም ሳይደክሙ የማይገኝ ነገር ስለ ሆነ ፤ ትምህርትን በምትማሪበት ጊዜ ፡ ሁሉንም መማር አለብሽ እንጂ ፤ ከበድ ከበድ ያለውን ትምህርት አይገባኝም ! እያልሽ ፡ ከተውሽውማ ፤ ምኑን ተማርሽው ፡-

ባለቤቱ ፡ ያቃለለው አሞሌ ፡ ባለ ዕዳው አይቀበለውም ።

ሰም ፡ ባለቤቱ ፡ መጠኑ ትንሽ ፡ መልኩ ጥቁር ፡ ጣዕሙ የማያሰማ ፡ በጣም ያልተጣራ ነው ፤ እያለ የናቀውንና ያቃለለውን አሞሌ ባለ ዕዳው ግምቱ በቂ ነው ብሎ አይቀበለውም ።

ወርቅ ፡ የቋንቋው ባለቤት የሆነ መንግሥት ፡ የናቀውንና ችላ ያለውን ቋንቋ የውጪ አገር ሕዝብ ይጠቅመኛል ብሎ ፡ ሊማረው ፡ ሊያከብረውና ሊወድደው አይችልም ።

አያድሩበት ቤት ፡ አያምሻሹበት ።

ሰም ፡ ልብን ከሐሳብ አሳርፎ ፡ ሰውነትንም አዝናንቶ እፎይ ! በማለት ፡ የማያድሩበት ቤት ፡ ሊያም ሻሹበት ከቶ አይገባም ፤ ምክንያቱም ፡ ከመሸ ወዲያ ፤ በጨለማ እየተደናበሩ ወደሚያድሩበት

ቤት ቢሄዱ ፤ ባመሸው ሰው ፈንታ ሌላ ተተክቶ ፡ ራቱ ተበልቶ ፡ መብራቱ ጠፍቶ ፡ በራፉ ተዘግቶ ይቁይና ፡ ትርፉ ከዚያም ከዚህም ሳይሆኑ በማሳል ሜዳ መቅረት ብቻ እንዳይሆን ነው።

ወርቅ ፡ ለሁሉም የሚቻል ቢሆን ኖሮ ፤ ይህን በእንግዳ ማረፊያ ቤት የሚመሰለውን ኃላፊና ጊዜያዊ ዓለም ቁርጠኛ ሆኖ በማያልፈውና በሚያዛልቀው በመንግሥተ ሰማያት ሊለውጡት እንጂ ፤ በማይረባ ነገር ሊልከሰከሱበት ፡ ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ሊጣሉበት ከቶ ባላስፈለገም ነበር ።

መሳምን ወድደሽ ፡ ጢምን ጠልተሽ ።

ሰም ፡ ከሁለቱ አንዱን ብቻ መርጠሽ ያገር እንጂ ፤ መሳምን ወድደሽ ጢምን ጠልተሽ እንዴት ይሆናል ፡-

ወርቅ ፡ ከሁለቱ አንዱን ብቻ መርጠሽ መያዝ አለብሽ እንጂ ፤ ትምህርትን ፈልገሽ ፡ ጥናትን ጠልተሽ ደንበኛ ተማሪ ለመሆን እንዴት ይቻላል ፡-

ፍየል ከመድረሷ ! ቅጠል መበጠስዋ !

ሰም ፡ ፍየል ችኩል የቤት እንስሳ በመሆንዋ ምክንያት ከቦታው ላይ ከመድረስዋ ወይም እንደደ

ምግብ ተቀምሶ ባለሞያ ትኹን አትኹን ስለማ ይታወቅ ፤ ኹሏም ሴት ትባላለች ።

ወርቅ ፡ መከራ ሳይመጣ በፊት ፤ ታማኝ መሆን አለ መኾኑ ስለማይታወቅ ፤ ኹሉም ጓደኛ ይባላል እንዲሁም ፈተና ሳይመጣ በፊት ፤ ጐበዝ ወይም ሰነፍ መሆን አለመኾኑ ስለማይታወቅ ፤ ሁሉም ተማሪ ይባላል ።

እባብን ያየ ፡ በልጥ በረየ ።

ሰም ፡ ድንገት እባብን ያየ ሰው ፡ ልክ ያየውን አስ ፈሪ እባብ ስለ መሰለው ፤ በፍርሃት ደነገጠና ልጥ አይቶ አውሬን እንዳየ እንስሳ በረገገ ።

ወርቅ ፡ ምቀኛና ፡ ተንኰለኛ ያጋጠመው ሰው ፡ የቀ ረውም ሰው ሁሉ ያው ስለሚመስለው ፤ እንደ ዱር አውሬ ይሸሻል እንጂ ፤ ማንንም አይጠጋም ።

ላም ባልዋለበት ፤ ኩበት ለቀማ ።

ሰም ፡ ላም (ከብት) ባልዋለበት ቦታ ላይ ኩበትን አገ ኛለሁ ብሎ ለቀማ መኼድ ትርፉ ከንቱ ድካምና ሥራ መፍታት ብቻ ስለ ሆነ ፤ የሚገባና ትክ ክለኛ ተግባር አይደለም ።

ወርቅ ፡ አጥፊው ሌላ ሆኖ ሳለ ፡ በችኰላ እርሱ ሳይ ሆን አይቀርም በማለት ንጹሑን ሰው ባልዋለ

ረሰች ወዲያው ከቤት አትክልት መካከል የጌ ሾም ሆነ የሎሚ ፡ የትርንጎም ሆነ የበኩረ-ሎሚ ፡ የብርቱካንም ሆነ የሮማን ፡ የዳማ ከሴም ሆነ የጤና አዳም ቅጠልን መበጠስዋ የተለመደ ስለ ሆነ ፤ እረኛዋን ታስገርፋለች ። ጌቶችዋንና ጐረቤቶቻቸውን ታስመርራለች ።

ወርቅ ፡ ቀላል ሰው ፡ ማንኛውንም በወረት ለመውደ ድና ለመጥላት ችኩል ከመሆኑ የተነሣ ፡ የማያ ውቀውን ሰው ገና ከማየቱና ከማግኘቱ ልምድ አርጎት ፡ ከቤተ ሰቦቹ መካከል እንዳንዱ ይሆ ንና ሳይጠይቁት ያማክራል ። እንደ አብሮ አደ ግም ይቀልዳል ። ከዚያም በኋላ ይህን ስጠኝ ፤ ያንን አውሰኝ ፤ እያለ ሰውን ማስቸገሩ የታወቀ ነው ። በመጨረሻውም ሁሉንም አስቀይሞና ራሱም አኩርፎ ዘሩንም አስነቅፎ ፡ አንድያውን ተለይቶ ይኼዳል ።

ዝናብ ሳይመጣ ፤ ኹሉ ቤት ፤ እንግዳ ሳይመጣ ኹሉ ሴት ።

ሰም ፡ ዝናብ ሳይመጣ በፊት ፤ ማፍሰስ አለ ማፍ ሰሱ ስለማይታወቅ ፤ ሁሉም ቤት ይባላል ። እንዲሁም እንግዳ ሳይመጣ በፊት ያዘጋጇችው

በት ነገር መጣላትና ማጉላላት ፤ ለቅጣትም አሳልፎ መስጠት ከፍ ያለ ስሕተት ነው ።

ሌባ እናት ፡ ልጅዋን አታምንም ።

ሰም ፡ ሌባ እናት ሌላውን ሰው ይቅርና ፤ የወለደችውን ልጅዋን እንኳን « አይሰርቅም» ብላ አታምንም ፤ ምክንያቱም ያው እንደ ራስዋ ስለሚመስላት ነው ።

ወርቅ ፡ ሴሰኛ ሰው ፡ ሌላውን ማመኑ ቀርቶ ሕጽው የሆነውን ጓደኛውንም እንኳ ፈጽሞ አያምንም ፤ ምክንያቱም የራሱን ተግባር ምሳሌ ስለሚያደርግ ነው ።

ግዛኝ ፤ ብለው ፡ ሊሸጠኝ አሰበ ።

ሰም ፡ «ታማኝና ቅን አገልጋይ እሆንህ ዘንድ ግዛኝ ብዬ ብለው ፤ እሺ ! በማለት ፈንታ ማቃለሉ ነው መሰለኝ ፤ ደላላ ሆኖ ለሌላ ሰው ሊሸጠኝ አሰበ ።

ወርቅ ፡ ብወደው « እኩያህን ፈልግ » ማለቱ ነው መሰለኝ ! እርሱም በበኩሉ እኔን በፍቅሩ እንደ መግዛት ችላ አለኝ ። ባከብረውም በማክበር ፈንታ ፤ ግርምቢጥ ናቀኝ ፤ ጣል አረገኝ ማለት ነው ።

በቅሎ ለኮዋን በጠሰች ፤ በራስዋ አሳጠረች ።

ሰም ፡ በቅሎ ለኮዋን በጠሰች ብሎ ቢነግረው ፤ ስትሳብ መጐተቻዋ ስትቆም ማሠሪያዋ ፡ ሣርን ስትግጥ መቀየጇዋ ፡ ጠፍር ስለሆነና ፡ መዝናናትም ስለ ቀረባት ፤ በራስዋ አሳጠረች ፤ አለው ይባላል ።

ወርቅ ፡ ዓቅሙንና ጥቅሙን የማያውቅ ሰው የበላይ አለቃውን ቢጋፋ ፤ ወይም ታዳጊውን ቢበድል፤ ከፍተኛ ጥቃትንና ጉዳትን በራሱ ላይ እንደ ፈረደ ይቆጠራል ። ማለት ነው ።

ቢከማች ፤ ዕዳው ፡ ካንች ፤

ሰም ፡ ዕዳው ቢከማች ፤ የኋላ ኋላ ካንቺ ራስ ስለማ ይወርድ መድኃኒቱ በየቀኑና ጥቂት በጥቂት ለባለቤቱ መክፈል ብቻ ነው ።

ወርቅ ፡ አንተን በሚመለከት የጋራ ጉዳይ ተፎካክረህ ለጊዜው ችላ ብትል ፤ የማታ ማታ ችግሩ ስለማይለቅህ ፤ ማድረግ ያለብህ ፤ በጊዜው ጉዳዩን መፈጸም ብቻ ነው ።